# ለኦሮምያ ክልል ልዩ ጥቅም ለመወሰን የወጣ አዋጅ ረቂቅ ምላሽ፤ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልዩ መልእክት

**ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር** **ግንቦት ፪ ፪ሺ፱ May 10, 2017**

የዚሁ ረቂቅ አዋጅ ሙሉ ርእስ "የኦሮምያ ክልል በፊንፍኔ/አዲስ አበባ ላይ ያለወን ሕገ-መንግስታዊ ልዩ ጥቅም ለመወሰን የወጣ አዋጅ ረቂቅ" ነው። አዋጁ ከወቅታዊ፡ ታሪካዊና፡ የኢትዮጵያ አንድነትና ሃገራዊ ጥቅም አንፃር ሲታይ እጅግ በጣም አደገኛ ስለሆነ ከወዲሁ የኢትዮጵያ ፓርላማ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ውድቅ እንዲያደርጉት እማፀናለሁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባጠቃላይ፤ የአዲስ አበባ ኗሪዎች ደግሞ በተለይ አዋጁ እርስ በርስ የሚያናቁርና አንድነታቸውን የሚፈታተን እምቅ ኃይል እንዳለው ተገንዝበው እንዳይፀድቅ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ መቃወም አለባቸው።

ለምንድነው የአዋጁ ረቂቅ አደገኛ የሚሆኖው? ማንኛውም የመንግስት ፖሊሲ በጎሳ ፖለቲካ የተመሰረተ ከሆነ፡ ገና በእንጭጭነቱ ማወቅ እንኳ ባይቻልም የኋላ ኋላ ግን ከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስና ምስቅልቅል እንደሚያመጣ ከብዙ አገሮች ተመክሮ መገንዘብ ይቻላል። ይህ ስለሆነም ኢትዮጵያ አገራችን ባላስፈላጊ የጎሳና የጎጥ ፖለቲካ ማጥ ውስጥ እንዳትገባና እንዳትታመስ ከሚል ስጋት የዛሬ ፪፪ (ሃያ ሁለት) ዓመት ETHIOPIA: The Political Economy of Transition በተሰኘው መጽሐፌ ውስጥ የሚከተለውን ሐሳብ አቅርቤ ነበር፡-

The TGE's [Transitional Government of Ethiopia] policy of *Kilil* and self-determination is commendable, but the consequence of fragmentation as a result of new wave of ethnic political consciousness, and the inability of some minority nationalities to become economically and politically viable would ultimately preoccupy Ethiopians to otherwise unforeseen problem.

የዛሬ ፪፪ ዓመት የፃፍኩትን መጣጥፍና በዛን ጊዜ ላስተላልፈው የፈለግኩትን መልእክት አሁን በኢትዮጵያ እውን ሆኗል። ምልአተ ሕዝቡ ከአገር-አቀፍ ንቃተ ኅሊና ወደ ክልል ከዛም ለጥቆ ወደ አውራጃና መንደር ዘቅጧል። ከአገር ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራ) ደግሞ በዚሁ ረገድ ብጥስጥሳቸውን ወጥተዋል። እጅግ የሚያሳዝንና የሚያሳስብ ጉዳይ ነው።

በርግጠኝነትና በግልፅ ከተናገርን ግን የዚሁ የጎሳ ፖለቲካ ጽንሰተ-ሐሳብ የተጀመረው በኢሕአዴግ ሳይሆን ከ፮፮ አብዮት ፍንዳታ በፊት በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የፈለቀ ነው። በዛን ጊዜ ተማሪዎቹ ለሃገራችው ቀናኢ፤ ለሕዝባቸው ተቆርቋሪ ስለመኖራቸው አንድም ሁለትም የለውም። ነገር ግን የብሔር ጥያቄን አስመልክቶ ከመጠን በላይ በማጋነንና አላስፈላጊም "የብሔሮች የራስ በራስ የመወሰን ዕድልና እስከ መገንጠል" የሚለውን መርሆ በማስተጋባት ብቻ የሚያስከትለውን አሉታዊ የፖለቲካ ውጤት ማየት አልቻሉም ነበር። ተማሪዎቹ ለሃገራቸውና ለሕዝባቸው ላደረጉት ተጋድሎና መስዋእትነት ቢያስመሰግናቸውም ቅሉ የኢትዮጵያን አንድነት የሚሸረሽር መርሆ በማራመዳቸው ግን ያስከስሳቸዋል፤ እኔም ከነሱ አንዱ ስለነበርኩኝ ያስከስሰኛል።

የብሔር መብት እንዳለ ሆኖ ክልሎችን በቋንቋ መሸንሸን ግን ስሕተት መሆኑን ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሁፎቼ አቅርቤ ነበር። አንዴም ሁሌቴም ስሕተት መሥራት ምንም አይደለም፤ በየትም ሕብረተሰብ የሚከሰት ስለሆነም የሰው ባህርይ ነው ማለት እንችላለን። ደጋግሞ ስሕተት መሥራት ግን ለግዙፍ አደጋ የሚያጋልጥ ብቻ ሳይሆን መድኃኒት የማይገኝለት ነቀርሳም ሊሆን ስለሚችል "ከመዓቱ ይሰውረን" ብለን ብቻ የምናልፈው ሳይሆን ታሪካዊ ሐላፊነትም በመሸከም ስር ከመስደዱ በፊት በጋራ መመከት ይኖርብናል።

አሁን አንባቢው በቅጡ እንዲገነዘበውና እንዲረዳው የአዋጁ ረቂቅ ዋና ይዘት ከሞላ ጎደል በቅደም ተከተል አቀርባለሁ:-

ረቂቅ አንቀፁ ሕገመንግሥቱን በመንተራስ "አንቀፅ 49 ንኡስ አንቀፅ 5... አዲስ አበባ በኦሮምያ ክልል በመሆኑ ..." ብሎ ይጀምርና "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ ሪፑብሊክ ሕገመንግሥት ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የሚከተለውን ታውጇል" ብሎ በመቀጠል ወደ ዝርዝር ይገባል።

"አዲስ አበባ በኦሮሞ ክልል በመሆኑ" የሚለወን ሐረግ አራት ነገሮችን ይቃረናል:- 1) በሕገመንግሥቱና የኢሕአዴግ መንግሥት በፈጠረው የክልል ወይም የፌደረሽን ሥርዓት: አዲስ አበባ ራሷን የቻለች መስተዳድር ወይም ክልል (autonomous adminsirative region) ሆናለች። አዲሱ ረቂቅ ይኸንን የአዲስ አበባ ስልጣን ይጥሳል። 2) ረቂቁ የዛሬ መቶ ወይም መቶ ከሐምሳ ዓመታት በፊት የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪክ ብቻ የሚያንፀባርቅ እንጂ ከዛ በፊት የነበረውን ታሪክ በግምት ቢያስገባ ኖሮ ከፊንፊኔ በፊት ምን ዓይነት ከተማ ወይም መንደር ባካባቢው ነበር ከሚል ጥያቄ ተነስቶ ታሪካዊ ሐቁን  በፈተሸ ነበር። ከፖለቲካ-ኢኮኖሚ አንፃር ካየነው ደግሞ አርብቶ አደር ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ስለሚንቀሳቀስ እና ተቀማጭ (sedentary) ስላልሆነ ቋሚ ከተሞችን መመስረት አይችልም። በተጨማሪ የኦሮሞ ተወላጆች ወደ አዲስ አበባ (ፊንፊኔ) የመጡት ብሎም ወደ ጠቅላላ መሃልና ሰሜን ኢትዮጵያ የተጓዙትና መሬት ይዘውም የተቀመጡት ከ16ኛ ከፍለዘመን ጀምሮ ነው፤ የስልጣን ልውውጥ በተደረገ ቁጥር ደግሞ በከተማዋ የሕዝብ ኗሪዎች ለውጥ (demographics) ተከስቷል፤ ሰለሆነም 3) አዲስ አበባ አሁን ባለችበት ደረጃ የጠቅላላ ኢትዮጵያውያን ከተማ ናት፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔርና ብሔረሰቦች የተሰባሰቡባት ከተማ ስለሆነች የኦሮምያ ክልል አካል ናት ብሎ ማለት ከተማዋ ለምታስናግዳቸው ሌሎች ብሔሮች በከተማዋ ወስጥ የመኖር ሕጋዊነት የላቸውም እንደማለት ነው የሚቆጠረው። 4) አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ከተማ ከመሆኗ ባሻገር የአፍሪቃ ዋና ከተማም ናት፤ የአፍሪቃ አንድነት ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ስለተመሰረተ ከተማይቱ የሁሉም አፍሪቃውያን ዲፕሎማቶች መኖርያና መናኸርያ ናት። በተጨማሪም የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪቃ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ዋና መስርያ ቤት በአዲስ አበባ ስለተቆረቆረ በዚሁ መስርያ ቤት የሚሰሩ ከአህጉሩ የመጡ ባለሙያዎች ኗሪነታቸው በኢትዮጵያ ርእሰ ከተማ ነው። ከዚህም በላይ አዲስ አበባ የዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶችና ኢንቨስተሮች የምታስተናግድ ከተማ ናት። የአዋጁ ረቂቅ ከላይ የተጠቀሱትን አራት ዓበይት ክስተቶችን ሰለሚቃረንና ወደ ፊት ከመገስገስ ይልቅ ወደ ኋላ የሚጎትት ጽንሰ-ሐሳብ ስለሆነ ከወዲሁ ወድቅ መሆን አለበት።

በዚሁ የረቂቁ ርእሰ-ነገር ቁጥር 5 (የረቂቁ ቅደም ተከተል ቁጥሮች ዝብርቅርቃቸው የወጣ ነው) "'ልዩ ጥቅም ማለት' በሕገመንግሥቱ እውቅና ያገኙ የኢኮኖሚ፤ ማሕበራዊ፤ የባህል፤ የቋንቋ፤ የአስተዳደራዊ፤ የልማት፤የፖለቲካ፤ የአከባቢ ደህንነት፤ የንብረት መብቶች የመሳሰሉትን በልዩ ሁኔታ የኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት በአዲስ አበባ ላይ የሚያገኘው ጥቅም ማለት ነው" በማለት ይገልጸዋል። ይኸንን ርእሰ-ነገር

አስመልክቶ አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። እሺ የኦሮሞ ተወላጆች ልዩ ጥቅም ይሰጣቸው እንበል፤ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ግን ልዩ ጥቅም ማግኘት አይችሉም ነው ወይስ ከልዩ ልዩ ከፍላተ-ሃገራት ፈልሰው ወደ አዲስ አበባ ስለመጡ እንደ ኗሪዎቹ (በረቂቁ መሠረት ኦሮሞዎች መሆኑ ነው) እኩል መብት ሊኖራቸው አይገባም ነው። ይህ በጣም አደገኛ አዝማምያ ስለሆነ በትንሺ ኢትዮጵያ በሆነችው በአዲስ አበባ አላስፈላጊ የጎሳ ፖለቲካና ግጭት ሊፈጥር ስለሚችል ረቂቁ በፍፁም መተግበር የለበትም የሚል አቋምና አመለካከት ነው ያለኝ።

በቁጥር 7 ደግሞ "'የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች' ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከመመስረቱ በፊት ጀምሮ ነባር ኗሪ የነበሩ ወይም አሁንም በከተማው ኗሪ የሆኑ ኦሮሞዎች ማለት ነው" ይላል። ይህ አባባል ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት የኢትዮጵያን ታሪክ የሚቃረን ስለሆነ ወይ ተሻሽሎ ይቅረብ ወይም ደግሞ ከናካቴው ይሰረዝ። የዛሬይቱ አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ከተማ ናት፤ እንኳንስ አዲስ አበባ ይቅርና መለስተኛ ከተሞች እንደነ መቐለ፤ ባሕርዳር፤ ሐዋሳ፤ ሐረር ወዘተ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ከተሞች እንጂ የአንድ ብሔር መዲናዎች አይደሉም።

በንኡስ-ርእስ ቁጥር 5 (ስያሜ)፡ 1. የከተማው ስም ፊንፊኔ ከአዲስ አበባ ጋር እኩል መጠርያ ይሆናል፡ 2. የከተማው ሕጋዊ ስም በፅሑፍ ፊንፊኔ/አዲስ አበባ ተብሎ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል። በአዲስ አበባ ላይ ፊንፊኔ ቢጨመር ተቃውሞ የለኝም፤ አዲሱ ስያሜ ይኸን ያህል ለውጥ አያመጣም፡ አዲስ አበባ ቀርቶ ፊንፊኔ ይባል እስካልተባለ ድረስ። ነገር ገን የስሙም ለውጥ ቢሆንም በአዋጅና በፓርላማው አፅዳቂነት ብቻ ሳይሆን በአብዝሃ የኢትዮጵያ ሕዝብ (በተለይም በአዲስ አበባ ኗሪዎች) ድምፅ መወሰን አለበት። ሕዝቡ እንዲያደምጽ መለስተኛ ረፈረንደም ቢደረግ ለሁሉም ይበጃል። አንዳንድ ጊዜ መንግሥት በወሰነው ብቻ እርምጃ መወሰድ የለበትም፤ ለሕዝቡም ዕድል ይሰጠውና በአዋጅ ረቂቁ ላይ ድምፅ ይስጥበት፤ ምሁራኑም ይወያዩበት።

ንኡስ-ርእስ ቁጥር 7 ደግሞ የስራ ቋንቋን አስመልክቶ "የከተማው አስተደዳር የሥራና የኦፊሴላዊ ቋንቋ አማርኛና አፋን ኦሮሞ ነው" ይላል። ይህ ወዝግብ መፍጠሩ አይቀርም። ቅድም እንደተጠቀሰው አዲስ አበባ በሕዝብ ኗሪነት ረገድ ብዙ ለውጥ ስላደረገችና የኢትዮጵያ መናገሻ ሆናም ስላገለገለች፡ አማርኛ ደግሞ የኢትዮጵያ (አዲስ አበባም ጭምር) መስርያ ቋንቋ ሆኖ እንዲያገለግል በሕገመንግሥቱ ስለተደነገገ እንደበፊቱ ቢቀጥል ለሰላምም ለእድገትም ይበጃል።

በንኡስ-ርእስ ቁጥር 11 'ስለ አስተዳደራዊ ጥቅሞች' አስመልክቶ "በከተማው መስተዳድር ም/ቤት...25% የማያንስ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ብቻ የሚወከሉበት መቀመጫ ይኖራቸዋል" ይላል። ኦሮሞ ያልሆኑ የከተማዋ ኗሪዎችስ ምን ያህል መቀመጫ ይኖራቸዋል? መስፈርቱስ ምንድነው? በከተማይቱ ምከር ቤት ተወካይነት አድልዎ ከተደረ ከፖለቲካ ኩርፍያ ወደ ዓመጽ ሊያመራ ስለሚችል ረቂቁ ባይተገበር የተሻለ ነው የሚል እምነት አለኝ።

አዲስ አበባ ከቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ብሔሮች ያቀፈች ከተማ ስለነበረች በአንዳንድ ሰፈር ቅይጥ ብሔሮች ሲኖሩባት በሌሎች ሰፈሮች ደግሞ የአንድ ብሔር አብላጫነት የሚታይበት ነበር። ለምሳሌ እኔ በኖርኩበት በስድስት ኪሎ አከባቢ እና ኩታ ገጠም በሆኑት ሌሎች ሰፈሮች እንደ አራት ኪሎ፡ ፒያሳ፡ ደጃች ውቤ ሰፈር ወዘተ የሁሉም ብሔሮች ሰፈር ነበሩ ማለት ይቻላል። በስድስት ኪሎና እንጦጦ ግርጌ ማለትም በሽሮ ሜዳ ደግሞ አብዝሐው ኗሪ የዶርዜ ብሔረሰብ ነበሩ። በተመሳሳይ መልኩ ተክለሃይማኖት

እና ፖፖላሬ የትግርኛ ተናጋሪ አብዝሐነት ሲታዩባቸው ማርካቶ ደግሞ የጉራጌ እና የአደሬ መናኸርያ ነበሩ ማለት ይቻላል፤ ጉራጌዎች ግን በማርካቶ ብቻ ሳይወሰኑ በጠቅላላ አዲስ አበባ በንግድ ተሰማርተው ይኖሩ ነበር። ሆኖም ግን በማርካቶ ውስጥ በርካታ ከወሎ፡ ከጅማ፡ ከሐረር የመጡ ኢትዮጵያውያን እስላሞች ኗሪዎች ነበሩ። የድሮ ሱማሌ ተራ ተክለሃይማኖት አጠገብ ነበር፤ የአሁኑ ሱማሌ ተራ ደግሞ ቦሌ ሩዋንዳ በተሰኘው ሰፈር ነው የሚገኘው። ሱማሌዎቹ ታድያ ከሌሎች ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ብሔሮች ጎን ለጎን ነው የሚኖሩት። የአማራ ብሔር ተወላጆች ደግሞ በጠቀላላ አዲስ አበባ ተዘርግተው ይኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ከተማይቱ አማርኛ ተናጋሪ ስለነበረች ብሔር ከብሔር የማይለይበት ጊዜ ነበር። ባለፉት ሁለት ዓሰርት ዓመታት ደግሞ አዲስ አበባ ከነበረችበት ሦስት እጥፍ አድጋለች፤የኗሪዎቿ ቁጥርም በዛው መጠን ወደ አራት ሚልዮን ተጠግቷል፤ ከዚህ ቀደም እምብዛም የማይታዩ ብሔረሰቦች እንደነወላይታ የመሳሰሉ አሁን በከተማይቱ በበርካታ ሰፈሮች ይታያሉ። ኢትዮጵያ ባጠቃላይ አዲስ አበባ ደግሞ በተለይ እንኳንስ ለራሳቸው ሕዝብ ለማንም ባዳ የሚያስተናግዱ ከሆነ የሚያስደንቅ አይሆንም።

ቦሌ ራሱ የአዲስ አበባ አዲስ ከተማ ከሆነ ቆይቷል፤ በስፋትም በውበትም እጅግ በጣም የተቀያየረው ቦሌ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ንኡስ ከተማ ነው። የአዲስ አበባ ዕጣ ፈንታ ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔሮች ለማቀፍና ለማስተናገድ ስለሆነና የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጎን ለጎን በሰላምና በመከባበር ለመኖር ስለፈቀዱና ስለሚፈልጉ ይህ ታሪክ ያመጣውን የብሔሮች ውህደት ለአንድ ብሔር ልዩ ጥቅም ተብሎ መደፍረስና መናወጥ የለበትም።

በዚሁ ንኡስ ቁጥር 11 ቁጥር 6 "ፊንፊኔ/አዲስ አበባ የኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት ዋና ከተማ ሆና ታገለግላለች" የሚለውን የፓርላማ አባላት መቀበል የለባቸውም። የኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት ከተማ አዳማ ናት፤ የእልህ ፖለቲካ ለመሰንዘርና ለማስፋፋት ካልሆነ በስተቀረ አዳማ የኦሮሞ ክልል ዋና ከተማ ሆኖ ትቀጥል፤ አዲስ አበባ ደግሞ እንደወትሮው የኢትዮጵያና የአፍሪቃ ዋና ከተማ ሆና ትቀጥል። በነገራችን ላይ "አዲስ አበባ የኦሮምያ ክልላዊ መንግሥት ዋና ከተማ" የሚለውን ሐሳብ አሁን በአዋጅ ረቂቁ የፈለቀ ሳይሆን ከ1997 ዓመተምህረት ኢትዮጵያ ወይም በአውሮጳውያን አቆጣጠር 2005 ምርጫና በኢሕአዴግና ቅንጅት የፖለቲካ ግጭት ከተፈጠረ በኋላ የመጣ አስተሳሰብ ነው። በዛን ጊዜ እንዳሁኑ በአዋጅ ሳይሆን በመንግሥት ባለስልጣናት ዙርያ በተብለጠለጠ ሐሳብ መሠረት አዲስ አበባ የኦሮምያ ከተማ ለማድረግ ተሞኩሮ ነበር፤ እቅዱ ለመተግበርም ያህል የኦሮምያ ክልል ፕረዚደንት ዋና ጽሕፈት ቤት ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ በማዛወር ጽ/ቤቱ ቦሌ ወስጥ እንዲሆን ተደርጎ ነበር። አሁን እንደገና የፖለቲካ ቀውስ ለማርገብ ተብሎ አዲስ አበባ የኦሮምያ ክልል ከተማ ይሆናል ብሎ ከተወሰነ ለቀውሱ ፈውስ ሳይሆን በሽታ ሊሆን ስለሚችል ቢታሰብበት መልካም ነው።

ንኡስ ቁጥር 12 'ስለ ማህበራዊ የአገልግሎት ጥቅሞች' በሚመለከት ሆኖ በዚሁ ርእስ ሥር ቁጥር 4 "በከተማው አስተዳደር ውስጥ ነዋሪ ለሆኑ የኦሮሞ ተወላጆች ልጆቻቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በአፋን ኦሮሞ የሚያስተምሩ ት/ቤቶች በመስተዳድሩ ውስጥ ተሰርተው ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል" ይላል።

በመርህ ደረጃ በአፍ ቋንቋ ልጆች እንዲማሩ ማድረግ ተቃውሞ ሊኖር አይችልም። እንድያውም ይህ ዓይነት ፖሊሲ፤ በተለይም ሁሉንም ብሔር ያካተተ ከሆነ፤ ከሕዝቡ ድጋፍ ማግኘቱ አያጠራጥርም። ነገር ግን በአንድ ከተማ ለአንድ ብሔር ጥቅም ብቻ ተብሎ ልዩ ትምህርት ቤት መፍቀድ ውህደትን አዳክሞ ልዩነቶችን መጋበዝ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የከተማዋ ኗሪዎች የሆኑት ሌሎች ብሔሮች "ለኛም ተመሳሳይ መብት ለምን አይሰጠንም" የሚል ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ። የኋላ ኋላ አሁን ማየት

የማንችላቸው ግን ለወደፊት ከፊታችን የሚደቀኑ ጎጂ ክስተቶች ሊያጋጥሙን ይችላሉ፤ ወይም ለመጭው ትውልድ አስፈሪ ቅዥት ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላ ረቂቁ በግምት ያላስገባው ነገር ቢኖር በስመ ልዩ ጥቅም ኦሮሞዎቹ ተነጥለው እንዲማሩ ከተደረገ ከሌሎች ብሔሮች የሚቀስሙትን ተሞክሮ ይቀርባቸዋል። ለምሳሌ በአንደኛ ደረጃ የኦሮሞ ልጆች ተማሪዎች ለብቻቸው ተነጥለው ከተማሩ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ በሚጓዙበት ጊዜ የመፎካከርና የመወዳደር ኃይላቸው በጣም ሊቀንስ ይችላል፤ የእውቀት ግንዛቤቸው ደግሞ ሊዳከም ይችላል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የስነ-ትምህርት ሊቃውንት በጥናትና ምርምር የደረሱበት ነገር ቢኖር ከተለያዩ መደብ: መነሻ: ጎሳ: ባህል: ወዘተ የመጡ ተማሪዎች በአንድ ትምህርት ቤት ወይም መማርያ ክፍል የሚማሩ ከሆነ ከመደበኛው ትምህርት በተጨማሪ ለአያሌ ተሞኩሮዎች ስለሚጋለጡ መጠነ-ሰፊ እውቀት ይኖራቸዋል፤ አንድ ወጥ ያካተተ ትምህርት ቤት ግን ተማሪዎቹን ለዝቅተኛ የእውቀት ግንዛቤ ከመዳረጉም በላይ ለጠባብ ብሔርተኛነት ስሜት ደግሞ ይገፋፉቸዋል። ስለሆነም የአዋጁን ረቂቅ ያቀረበውን ኢርትዓዊ የልዩ ጥቅም ሐሳብ ለመቃወም ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ወጣት ተማሪዎችም ከፋኛ እንዳይጎዱ ለማሳሰብም ጭምር ነው።

በዚሁ ንኡስ-ርእስ ቁጥር 32 (‘ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች’) ደግሞ “ይህን አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ፤ መመርያ፤ የአሠራር ልምዶች ወይም ውሳኔዎች በዚህ አዋጅ ወስጥ የሚደነገጉ ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም” ይላል። የአዋጁ ረቂቅ ለማሻሻል ወይም ለማከል ሳይሆን ያነጣጠረው የነበሩት ሕጎች ለማጥፋት ነው የተነደፈው ማለት ይቻላል። መንግሥት ሰከን ብሎ ነገሮችን ያላመጠ አልመሰለኝም። ኢትየጵያ ባሁኑ ጊዜ በልማት ጎዳና አመርቂ ስኬቶችን እያከናወነች ባለችበት ሰዓትና አያሌ የውጭና የውስጥ ጠላቶች በሚተናኮሉባት ወቅት ይህ አላስፈላጊ አዋጅ በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ ሊሆን ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ወይ መንግሥት ራሱ ረቂቁን አሻሽሎና አርሞ ያቅርብ ወይም ደግሞ ፓርላማው ረቂቁን ውድቅ ያድርገው። አለዛ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአዲስ አበባ ኗሪ ተቃውሞውን ማሳየት አለበት።

**የዚህ ፅሑፍ አዘጋጅና የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ) የባለቤትነት መብት በሕግ የተደነገገ ነው። All Rights Reserved Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA) ለትምህርታዊና ገንቢ አስተያየት ለደራሲው በሚከተለው አድራሻ መልእክት መላክ ይቻላል፦**
[dr.garaia@africanidea.org](mailto:dr.garaia@africanidea.org)